# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

??/? /??? 216525
?? 25/11/2014 ?/?

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)
ቀነዓ ቂጣታ
ፈይሳ ወርቁ
ደጀኔ አያንሳ
ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- 1.አቶ አዲያን ሀ/መህዲ 2. ሳቢት ሀ/መህዲ 3. ለይን ሀ/መህዲ 4. ለቢባ ሀ/መህዲ 5. ቶፊቅ ሀ/መህድ 6. መሀመድ ሀ/መህዲ 7. **ወ/ሮ** አለይኬ ደማም 8. አቡዱረሂም ሀ/መህድ 9. ረቢዳ ሀ/መህዲ 10. አሊያ ሀ/መህዲ 11. **ወ/ሮ** ሉባባ ሀ/ፈረጃ 12. ሙንተሀ ሀ/መህዲ 13. ሰልማ ሀ/መህዲ 14. ሳራ ሀ/መህዲ 15. ሙኢና ሀ/መህዲ 16. ዋህቢያ ሀ/መህዲ 17. ነጂያ ሀ/መህዲ 18. ሰዓዳ ሀ/መህዲ 19. ሮይዳ ሀ/መህዲ 20. **ወ/ሮ** በቱላ የሱፍ 21. ሱሪያ ሀ/መህዲ 22. አብዲ ሀ/መህዲ 23. መሀመድ ሀ/መህዲ 24. ለሚያ ሀ/መህዲ 25. ወ/ሮ ሱመጌ አብዱልሰላም 26. ሰመሪያ ሀ/መህዲ 27. ሳዲያ ሀ/መህዲ 28. ነጂብ ሀ/መህድ 29. ሙዲር ሀ/መህዲ 30. **ወ/ሮ** ሙንተሃ ሽፋ 31. ዚያዳ ሀ/መህዲ 32. ቀቢላ ሀ/መህድ 33. መዘረዲን ሀ/መህዲ 34. አቶ አብድልባር ሀ/መህዲ 35. ዘይቱና ሀ/መህዲ - 22 ኛ ተጠሪ ቀረቡ ሌሎች አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- 1. ወ/ሮ ሉባባ ሀ/አደም 2. አቶ ሰልማን አማን - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካቾች ህዳር 13 ቀን 2014 ዓ/ም በተፃፈ አቤቱታ የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 16860 ነሀሴ 19 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 156223 ሚያዝያ 26 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታቸውን በማቅረባቸው ነው፡፡ ቅሬታቸውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካቾች የሚቃወሙባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልን ይገባል የሚሉትን ዳኘነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የስር ፍ/ቤቶች በአልከሶ ከተማ ውስጥ የሚገኘውን 408 ካ/ሜ ባዶ ቦታ ለተጠሪ ልጅ አቶ ምንወር ሀ/መህዲ ሟች

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ስጦታ አድርጎለታል የተባለው ንብረቱ ከሌሎቹ አምስት ሚስቶቹ ጋር ያፈራው ሆኖ እያለ እና የሌሎቹ አምስት ሚስቶቹ ፍቃድ ሳይኖርበት የተደረገ ስጦታ በመሆኑ ውድቅ መሆን ሲገባ፤ በአልከሶ ከተማ ውስጥ በ464 ካ/ሜ ቦታ ላይ ያረፈው ቤት ሟች ከአምስቱ ምስቶቹ ጋር በጋራ ያፈራው ንብረት ሆኖ እያለ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ብቻ ግማሽ ድርሻ እንድትካፈል መወሰኑ፤ በአልከሶ ከተማ ውስጥ በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው 266.5 ካ/ሜ የከተማ ቦታ ውሳኔው ግልጽነት የጎደለውና የጋራ ንብረታችን ሆኖ መወሰን ሲገባ መታለፉ፤ በአልከሶ ከተማ ውስጥ የሚገኘው በ310 ካ/ሜ ቦታ ላይ ያረፈው ቤት ሟች ለመስጅድ አግልግሎት የሚጠቀምበት ስለመሆኑ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ሳታስተባብል እና ሟችን ሳታገባ በፊት የተፈራ ንብረት መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ታልፎ ግማሹ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ድርሻ ነው በሚል መወሰኑ፤ በኢሉስ ከተማ ውስጥ የሚገኝ በ125 ካ/ሜ ቦታ ላይ ያረፈው ቤት ሟች በህይወት እያለ የተፈራ ንብረት ሆኖ እያለ በስሟ በመመዝገቡ ብቻ የግል ንብረቷ ነው ተብሎ መወሰኑ እና በሚቶ ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኘው መሬት ሟች 1ኛ ተጠሪን ከማግባቱ በፊት የተፈራ ንብረት መሆኑና አመልካቾች አብረን ስንጠቀምበት የቆየን መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ታልፎ የግሏ ንብረት ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልን የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን ከ1ኛ እስከ 6ኛ ያሉት አመልካቾች ሲሆን ተከሳሽ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ነች፡፡ የአሁን ከ7ኛ እስከ 35ኛ አመልካቾችና 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብዎች ሆነው ተከራክረዋል፡፡ ከሳሾች ባቀረቡት ክስ ወላጅ አባታችን በ29/5/2006 ዓ/ም ሞቷል፡፡ የአባታችን የውርስ ንብረት በአልከሶ ከተማ ውስጥ የሚገኙ በ310 ካ/ሜ ቦታ ላይ ያረፈ ቤት፣ በ300 ካ/ሜ ቦታ ላይ ያረፈው ቤት፣ 408 ካ/ሜ የሆነ ባዶ ቦታ፣ በኢሉስ ከተማ ውስጥ የሚገኝ በ125 ካ/ሜ ላይ ያረፈው ቤት እና በሚቶ ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ 3 ሄክታር መሬት የጋራ ንብረታችን በመሆኑ ድርሻችንን ታካልለን ሲሉ ጠይቀዋል፡፡ ተከሳሽም የአሁን 1ኛ ተጠሪ በአልከሶ ከተማ ውስጥ የሚገኘው በ310 ካ/ሜ ቦታ ላይ ያረፈው ቤት እኔና ሟች ብቻ የፈራነው ንብረት በመሆኑ ከሳሾችን የሚመለከት አይደለም፡፡ በ300 ካ/ሜ ቦታ ላይ ያረፈው ቤት የግል ንብረቴ ነው፡፡ 408 ካ/ሜ የሆነ ባዶ ቦታ ለአቶ ምንወር ሀ/መህድ የተሰጠ ነው፡፡ በኢሉስ ከተማ ውስጥ የሚገኘው በ125 ካ/ሜ ላይ ያረፈ ቤት ለአቶ ሰለማን አማን የተሸጠ በመሆኑ የውርስ ንብረት አይደለም፡፡ በሚቶ ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ 3 ሄክታር መሬት የግሌ ንብረቴ ሲሆን ከሳሾችም የራሳቸው መሬት ያላቸው በመሆኑ ሊጠይቁኝ አይገባም ያለችና በከሳሾች እጅ ይገኛል ያለችውን በአልከሶ ከተማ ውስጥ የሚገኝ በ464 ካ/ሜ ቦታ ላይ ያረፈ ቤት እኔና ሟች ብቻ ያፈራነው በመሆኑ ደርሻዬንና የልጆቼን ድርሻ ይካፍሉኝ ስትል የጠየቀችና ሌሎቹንም በርካታ ንብረቶች በመዘርዘር የሚስትነት ድርሻዋ እና የልጆቿን ድርሻ ይወሰንልኝ ስትል ጠይቃለች፡፡ 1ኛ ጣልቃ ገብ ጣልቃ በኢሉስ ከተማ ውስጥ የሚገኘውን በ125 ካ/ሜ ላይ ያረፈው ቤት ከተከሳሽ ገዝቶ ቤት ሰርቶበት ይዞ እየተጠቀመበት ያለ በመሆኑ ከክርክሩ ውስጥ ይውጣልኝ ሲል የጠየቀ ሲሆን፣ ሌሎቹ ጣልቃ ገብዎች ደግሞ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ንብረት የግል ንብረታችን ነው የሚሉትን በመጥቀስ ከክርክሩ ውስጥ እንዲወጣላቸው፣ ከሟች ጋር በጋራ ያፈራነው ንብረት ነው የሚሉትን በመዘርዘር የሚስትነት ድርሻቸው እንዲካፈላቸው፣ የሟች ወራሾች ደግሞ የወራሽነት ድርሻቸች እንዲካፈለን ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 156223 ሚያዝያ 26 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ግራ ቀኙን ያከራከሩት ንብረቶች በአልከሶ ከተማ ውስጥ የሚገኘው በ300 ካ/ሜ ቦታ ላይ ያረፈው ቤት የተባለው፣ ይዞታው 266.5 ካ/ሜ ሲሆን ሟች በፍላጎቱ ለማዘጋጃ ቤት በተከሳሽ ስም እንዲሆን አመልክቶ በስሟ የባለቤትነት ደብተር የተሰጣት በመሆኑና ሌሎቹም ምስቶች የየራሳቸው ቤት ያላቸው በመሆኑ የግል ንብረቷ ነው፡፡ በአልከሶ ከተማ ውስጥ 408 ካ/ሜ ባዶ ቦታ ለአቶ ምንወር ሀ/መህዲ የተሰጠ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ የውርስ ንብረት አይደለም፡፡ በአልከሶ ከተማ ውስጥ በ310 ካ/ሜ ቦታ ላይ ያረፈው ቤት ሟች እና ተከሳሽ ብቻ በጋራ ያፈሩት ንብረት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ግማሽ ድረሻ ለተከሳሽ ይካፈል ግማሹ የሟች ድርሻ ደግሞ ለወራሾቹ የሚካፋፈል ነው፡፡ በኢሉስ ከተማ ውስጥ የሚገኘው በ125 ካ/ሜ ቦታ ላይ ያረፈው ቤት ከሳሾችና ጣልቃ ገብዎች ለአቶ አዲያን ሀ/መህዲ የተገዛ የግል ንብረቱ ነው ሲሉ የተከራከሩ ቢሆንም ምስክሮቻቸው ቃላቸው የሚቃረንና የአቶ አዲያን ሀ/መህዲ የተሰጠ ስለመሆኑ ማስረዳት አልቻሉም፡፡

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ቤቱ በተከሳሽ ስም ተመዝግቦ የሚገኝና የተከሳሽ የግል ንብረት መሆኑን በተሻለ ሁኔታ ያስረዳች ስሆን፣ ጣልቃ ገብ አቶ ሰልማን አማን ገዝቶት ቤት ሰርቶበት ይዞት የሚገኝ በመሆኑ የውርስ ንብረት አይደለም፡፡ በሜቶ ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኘው መሬት ከሳሾችና ጣልቃ ገብዎች ሟች በምርቱ ያስጠቅሙን ነበር የሚል ክርክር ያቀረቡ ቢሆንም፣ ሟች ምርቱን ለተከሳሽ የሚወስዱ እንደነበረና በተከሳሽ ስምም ተመዝግቦ የሚገኝ ለሌሎቹ ምስቶች የገጠር መሬት አከፋፍሏቸው በተለያየ ቦታ የገጠር መሬት ይዘው እየተጠቀሙበት የሚገኙና የየራሳቸው ድርሻ ያላቸው መሆኑ በመረጋገጡ ይህ የተከሳሽ ድርሻ የግል ንብረቷ ነው፡፡ ሌሎች ንብረቶች ተከሳሽ በከሳሾች እጅ አሉ ያለቻቸው ንብረቶች በቡታጅራ ከተማ ውስጥ የሚገኘው የንግድ ቤት የሟች ንብረት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ በአልከሶ ከተማ ውስጥ የሚገኘው በ464 ካ/ሜ ቦታ ላይ ያረፈው ቤት ሟች እና ተከሳሽ ብቻ ያፈሩት ንብረት መሆኑ በመረጋገጡ ግማሹ የተከሳሽ ድርሻ ነው፡፡ ግማሹ ደግሞ የሟች ደርሻ ሲሆን ወራሾቹ የሚከፋፈሉት ይሆናል፡፡ ተከሳሽ ሌሎች ቤቶችና መሬቶች ዘርዝራ ድርሻዬ እና የልጆቼ ድርሻ ይካፈለኝ ስትል የጠየቀችውን በተመለከተ የሌሎቹ ጣልቃ ገብ ሚስቶች ድርሻ እና የግል ንብረታቸው መሆኑ በመረጋገጡ ከሳሽ ሊትካፈል አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካቾች ለደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ አቅርበው አከራክሮ በመ/ቁጥር 16860 ነሀሴ 19 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካቾች ለደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበው በመ/ቁጥር 17350 ጥቅምት 16 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ ጉዳዩ የፌደራል ፍ/ቤቶች ጉዳይ በመሆኑ ለማየት ስልጣን የለኝም ሲል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ በተለያዩ ከተማዎች ውስጥ ከሚገኙት ቤቶች መካከል ከሌሎቹ በ1ኛ ተጠሪ ስም በመሆናቸው ብቻ እንደግል ሀብት ተቆጥረው የሰበር አመልካቾች ሊካፈሉ አይገባም የተባለበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪዎች ጥር 25 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልን ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾችም የካቲት 17 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አሁን ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ምክንያት የሆኑት ንብረቶች በአልከሶ ከተማ ውስጥ የሚገኘውን 408 ካ/ሜ ባዶ ቦታ፣ በአልከሶ ከተማ ውስጥ በ464 ካ/ሜ ቦታ ላይ ያረፈው ቤት፣ በአልከሶ ከተማ ውስጥ በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው 266.5 ካ/ሜ የከተማ ቦታ፣ በ310 ካ/ሜ ቦታ ላይ ያረፈው ቤት፣ በኢሉስ ከተማ ውስጥ የሚገኝ በ125 ካ/ሜ ቦታ ላይ ያረፈው ቤት፣ በሚቶ ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኘው መሬት በተመለከተ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ሟች በህይወት እያለ አምስት ሚስቶች ያሉት ሲሆን ለአምስቱም ሚስቶቹ ንብረቶች አከፋፍሏቸው የየራሳቸውን ንብረት የመኖሪያ ቤትና መሬት ይዘው የሚገኙ መሆኑን፣ የአሁን 1ኛ ተጠሪም እንዲሁ የራሷን ቤትና መሬት ይዞታ የሚትገኝ መሆኑ ተረጋግጦ ውሳኔ የተሰጠ ስለመሆኑ የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡ የአሁን አመልካቾች ቅሬታ ያቀረቡበት ንብረቶች በጋራ ያፈራናቸው ንብረቶች መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የአሁን ተጠሪ የግል ንብረት መባሉና ከሟች ጋር ብቻ እንዳፈራች ተደረጎ ግማሹ እንዲካፈላት መወሰኑ ተገቢ አይደለም የሚል ሲሆን የስር ማስረጃ የመስማትና የመመዘን ሥልጣን የተሰጣቸው ፍ/ቤቶች የአሁን 1ኛ ተጠሪ የግል ንብረት የሆነውንና ከሟች ጋር በጋራ ያፈራችን ንብረቶች በስሟ ስለተመዘገበ ብቻ ሳይሆን በቀረቡት የሰነድ ማስረጃ እና የሰው ምስክሮች አጣርቶ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ እንዲሁም የአሁን 1ኛ ተጠሪ በጋራ ያፈራነው ነው ስትል እንዲካፈላት የጠየቀቻቸውን ንብረቶች በቀረቡት የሰነድ ማስረጃና የሰው ምስክሮች አጣርቶ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ለንብረቱ መፈራት አስተዋፆ እንደሌላትና የአሁን አመልካቾች የግል ንብረቶች መሆናቸውን አረጋግጦ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

*ማ ሳታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

በመ/ቁጥር 41526 ላይ በሰጠው ውሳኔ አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ ከማስረጃ ምዘና ጋር የተያያዘና የፍሬ ነገር ክርክር ላይ ያተኮረ ከሆነ በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የማይችል ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበት ይገኛል፡፡ በመሆኑም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ሥልጣን መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያልተሰጠው በመሆኑ የአመልካች ማስረጃ ምዘና አቤቱታ የመሠረታዊ የሕግ ስሕተት መመዘኛን ያሟላ ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## ውሳኔ

1. የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 16860 ነሀሴ 19 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 156223 ሚያዝያ 26 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. በሰበር ሰሚው ችሎት ጥር 2 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት በስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የመ/ቁጥር 18322 ላይ የተሰጠው የአፈጻጸም እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
4. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*